# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو


Gaafa: 01-10-2012 تاريخ

Lakk.: No.: 016/stm-abo/2012 رقم

## *ኢሬቻ በኣል ላይ ተይዘው የታሰሩት የኦሮሞ ተወላጆች ባስቸኩዋይ እንዲፈቱ*

### *(የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ)*

በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ተወላጆች በያመቱ በዚህ ወቅት ቡሾፍቱ ሃርሰዲ ሃይቅ ላይ በመገናኘት ታሪካዊውንና የኦሮሞነታቸው መለያ ባህል የሆነውን የኢሬቻ በኣል ያከብራሉ። ከኣውሮፓ፣ ከኣሜሪካና ከሌሎችም የኣለም ሃገሮች የሚመጡ በርካታ ቱሪስቶች ይህንን በኣል ኣስመልክተው በሚሰጡት ኣስተያየት "ኣፍሪካ ውስጥ ሚሊዮኖችን የሚያሳትፍ እንደ ኢሬቻ ያለ ኣስደማሚ በኣል ኣልታየም" በማለት የኢሬቻን በኣል ታላቅነት መመስከራቸውም ይታወቃል።

ኦሮሞ በግድ ኢትዮጵያዊነትን እንዲቀበል የሚያስገድዱ ስልጣን ላይ ያለው መንግስትም ሆነ ሌሎች ሃይሎች ግን የኦሮሞ ህዝብን ማንነት የሚያንጸባርቀውን የኢሬቻ በኣል በተመለከተ ደስተኞች ኣይደሉም። የራሳቸውን ባህልና ማንነት በግድ በኦሮሞው ላይ ለመጫን ከመሞከር በቀር ለዚህ የኦሮሞ ህዝብ ባህል ኣድናቆት ሊኖራቸው ቀርቶ ተገቢውን የህዝባዊ ባህልነት ስፍራ ሊሰጡት እንኩዋን ኣይፈልጉም። የኢትዮጵያ ገዢዎች ዛሬም ሆነ ትላንት ከኢትዮጵያ ኣልፎ ለመላው ኣፍሪካ ኣኩሪ የባህል ቅርስ የሆነውን የኢሬቻ በኣል መንግስታዊ እውቅና እንደነፈጉት ዘለቁ። ይሁን እንጂ እነርሱ ዘላለም ማንነቱን ማፈን የሚከጅሉትና ታላቅነቱን ለማሳነስ የሚደክሙት የኦሮሞ ህዝብ ካሁን ወዲያ በእግራቸው ስር ተንበርክኮ እንደማይገዛና የተደፈረውን የሃገሩንና የህዝቡን ነጻነት መልሶ ለመጎናጸፍ ዝግጁ መሆኑን እያሳየ ይገኛል።

የዘንድሮው የኢሬቻ በኣልም ባለፈው መስከረም 30, 2012 በቡሾፍቱ ሆራ ሃርሰዲ ሃይቅ ላይ እንደተለመደው ከተለያዩ የኦሮምያ ኣካባቢ የመጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኦሮሞ ዜጎችና የህዝቡ ወዳጆችን በማሳተፍ በድምቀት ተከብሮ ውሏል። ጸረ ኦሮሞ ህዝብ የሆነው የወያኔ መንግስት ይህንን በኣል ለማደናቀፍ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የታጠቀ ሃይል በማሰማራት እንደለመደው የበኣሉን ተሳታፊዎች የማሰር፣ የመደብደብ እንዲሁም የባህል ኣልባሳትና ጌጣጌጦችን ከኦሮሞ ወጣቶች ላይ የማውለቅና የመንጠቅ እርምጃ በመውሰድ ስርኣቱ ለኦሮሞ ህዝብ ያለውን ጠላት ነት ዘንድሮም ኣስመስክሯል። የታጠቁ የወያኔ ሃይሎች በሌሎች በኣላት ላይ የደህንነት ጥበቃ ኣገልግሎት ለመስጠት የሚሰማሩ ሲሆን የኦሮሞ ባህላዊ በኣል ላይ ግን የድብደባ፣ የዘረፋና የእስራት እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይሰማራሉ።

በዚህ የስርኣቱ ጠላታዊ እርምጃም ቁጥራቸው ከመቶ በላይ የሆነ የበኣሉ ተሳታፊዎች እዚያው ቡሾፍቱ ላይ መታሰራቸው ታውቆኣል። 55 የሚሆኑት ደግሞ ወደ ማእከላዊ እስር ቤት ተወስደው ከፍተኛ የሰቆቃ ተግባር እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ ተደርሶበታል። ይህ እንግዲህ እስካሁን በተገኙት መረጃዎች ብቻ የተረጋገጠ ሲሆን በኣላችሁን ለምን ኣከበራችሁ ተብለው የታሰሩት ዜጎች ቁጥር ከዚህ ኣሃዝ እንደሚልቅ ይታመናል።

በቀጣናችን ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚሰጡ የሚባሉና በሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ የገዘፈ ሽፋንበመስጠትየሚታወቁ ኣንዳንድ ሚድያዎች እንዲህ ባለው ሳቢ ባህላዊ ትይእንት ላይ በመቶ የሚቆጠሩ ዜጎች ተይዘው ሲታሰሩ፣ ሲደበደቡና በኣስሮች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ኣያዩ እንዳላዩና እየሰሙ እንዳልሰሙ መሆናቸው በርግጥ ኣሳፋሪና የሚያስተዛዝብም ነው። እንዲህ

ኣይነቶቹ ሚድያዎች ሆይ! በኦሮሞ ጥላቻ ኣይናችሁን ከመጨፈንና ጆሮኣችሁን ከመደንቆር ድናችሁ ለሁሉም ወገን እኩል የሚያገለግል ሚድያ እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናቀርብላችሁለን።

የወያኔ መንግስት ይህን መሰሉን እርምጃ ሲወስድ ይሄኛው የመጀመሪያው ባይሆንም የስርኣቱ እርምጃዎች በሙሉ ግን ህዝባችንን ተስፋ ኣስቆርጦት ወደ ሁዋላ ኣልመለሰውም። ነገም ወደ ሁዋላ ሊመልሰው በጭራሽ ኣይችልም። የባህል መብት ኣስከብረያለሁ የሚለው መንግስት ለምን ባህላዊ ስርኣታችሁን ኣከበራችሁ ብሎ በመወንጀል የኦሮሞ ተወላጆችን ኣፍሶ ማሰሩ የተስፋ መቁረጥ ምልክት ነው። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ይህንን ጸረ ኦሮሞ እርምጃ በጽኑ ያወግዛል። ስርኣቱ እስካሁን በዚህ ምክንያት በተለያዩ ቦታዎች ኣስሮ እያሰቃየ የሚገኘውን የኦሮሞ ተወላጆችም ባስቸኩዋይ እንዲለቅ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በኣጽንኦት ያሳስባል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

ጥቅምት 01, 2012